# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

# የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍልን ለማቋቋምና

# አሰራሩን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 127/2009

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ነሀሴ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 127/2009

ታክስ ከፋዮች በታክስ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉበት ተደራሽነት ያለው፣ በአግባቡ የተደራጀ እና የተቀላጠፈ ውሳኔ የሚሰጥ የታክስ የቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል በማቋቋም ቅሬታ ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታዎች የሚታዩበትን፣ የቅሬታ አቀራረብና ምርመራ፣ የውሳኔ ሃሳብ አቀራረብ፣ ውሳኔ አሰጣጥና ሥነ-ሥርዓት፣ የቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ሥልጣንና ተግባር የሚወስን መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

ባለሥልጣኑ በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ **"የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍልን ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 127/2009"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፦

   1) **"ባለሥልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፤
   2) **"ታክስ ከፋይ"** ማለት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ሲሆን በፌዴራል የታክስ አስተዳዳር አዋጅ አንቀጽ 2(41) በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) የተደነገጉትን ይጨምራል፤
   3) **"ኃላፊ"** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ የወከለው የዘርፍ ኃላፊ ወይም የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፤
   4) **"የሥራ ክፍል"** ማለት በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት የፌደራልና የአዲስ አበባ እንዲሁም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 55 (1) መሰረት የሚቋቋም የታክስ ጉዳዮች ቅሬታ አጣሪ ክፍል ነው፤

5) **"የውሳኔ ሀሳብ"** ማለት ታክስ ከፋዮች በሚያቀርቡት ቅሬታ ላይ በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ተጣርቶ ለዋና ዳይሬክተሩ ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ለወከለው ኃላፊ የሚቀርብ የውሳኔ ሀሳብ ነው፤

6) **"የታክስ ውሳኔ"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(34) ለታክስ ውሳኔ በተሰጠው ትርጉም ሥር በፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ሰ) ወይም (ሸ) የተመለከቱት ናቸው፤

7) **"ቅሬታ"** ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2(34) ለታክስ ውሳኔ በተሰጠው ትርጉም ስር በፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ረ)፣ (ሰ) ወይም (ሸ) የተመለከተና በታክስ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ የታክስ ከፋዮች ቅሬታ ነው፤

8) **"የታክስ ማስታወቂያ"** ማለት በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (35) በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ረ) እና (ሰ) የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፤

9) **"የታክስ ስሌት ማስታወቂያ"** ማለት በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (29) በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ረ) እና (ሰ) የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፤

10) **"የቅሬታ ማስታወቂያ"** ማለት በታክስ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ የታክስ ከፋዩ የቅሬታ ማመልከቻና ሌሎች ደጋፊ ሰነዶች ናቸው፤

11) **"የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን"** ማለት በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ (1) የተቋቋመው ይግባኝ በሚባልባቸው የታክስ ውሳኔዎች ላይ ይግባኝ የሚሰማ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ነው፤

12) **"አዋጅ"** ማለት የፌዴራል የታክስ አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፤

13) በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በታክስ ህግ የተሰጣቸው ትርጉም ይይዛሉ።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በፌዴራል የታክስ አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 983/2008 መሰረት በታክስ ውሳኔዎች ላይ በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የስራ ክፍልን ማቋቋምና ማደራጀት

4. **ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍልን ስለማቋቋም**

ባለሥልጣኑ በታክስ ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አጣርቶ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ የቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ያቋቁማል።

5. **የታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል አደረጃጀት**

1) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል፣

(ሀ) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል የጽ/ቤት ኃላፊ፣

(ለ) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ባለሙያዎች፣

(ሐ) የታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍሉ ፀሐፊ

(መ) የሪከርድ ሥራ አመራር ሁለገብ ባለሙያ፣

(ሠ) የጽህፈት ቤት ረዳት እና እንደ አስፈላጊቱ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል።

2) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል በዋና መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንደ አስፈላጊነቱ አንድና ከአንድ በላይ ሊደራጅ ይችላል፤

6. **ተጠሪነት**

1) በዋና መሥሪያ ቤት የሚቋቋመው የታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተሩ ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ለወከለው ኃላፊ ይሆናል፣

2) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚቋቋመው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ተጠሪነቱ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዋና ሥራ ስኪያጅ ይሆናል፣

7. **የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ሠራተኞች አመዳደብ**

1) የሥራ ክፍሉ ሠራተኞች በዋናው መ/ቤት በዋና ዳይሬክተር እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤት በማኔጅመንት አካል የሚመደቡ ይሆናል፤

2) በክፍሉ የተመደቡ ሠራተኞች ወይም የሥራ ክፍሉ ጽ/ቤት ኃላፊ ከአቅም በላይ በሆነ አስገዳጅ ምክንያት በሥራ ቦታ በማይገኝበት ጊዜ የሚመለከተው ኃላፊ በጊዜያዊነት ሊተካ ይችላል፤

## ክፍል ሦስት

## የታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

8. **የሥራ ክፍሉ ሥልጣን**

ክፍሉ የሚመረምራቸውን ጉዳዮች በተመለከተ፣

1) በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ታክስ ከፋይ የታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ21 (ሃያ አንድ) ቀናት ውስጥ በውሳኔው ላይ በጽሑፍ የሚያቀረበዉን የቅሬታ ማስታወቂያ ማመልከቻና ደጋፊ ሰነዶችን ተቀብሎ ይመረምራል፣

2) ባለሥልጣኑ የውሳኔ ማስታወቂያዎች እና የታክስ ስሌቶች በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በሚቀርብበት ጊዜ በባለሥልጣኑ የተፈቀደ ሰነድ መሆኑን በማረጋገጥ ይቀበላል፤

3) የሥራ ክፍሉ የቅሬታ ማስታወቂያ የቀረበበትን የታክስ ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ለመቀበል፣ ውድቅ ለማድረግ፣ ለማሻሻል የሚያስችል የውሣኔ ሀሣብ የማቅረብ ሥልጣን አለው፤

4) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅሬታ የቀረበበት የታክስ ውሳኔ በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ከሆነ የመጀመሪያውን የታክስ ስሌት በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በተደረገ ማሻሻያ ላይ ብቻ በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣

5) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በታክስ ከፋዩ የቀረበ ቅሬታ ማስታወቂያ ማመልከቻ በአግባቡ እንደቀረበ ተቆጥሮ በክፍሉ ተቀባይነት የሚኖረው፤

(ሀ) የቅሬታ ማመልከቻው ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔውን የሚቃወምበት ምክንያቶች፣ ታክስ ከፋዩ ውሳኔውን ለማስተካከል ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን ማሻሻያዎች እና እነዚህን ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት በትክክል የሚገልጽ ከሆነ፤

(ለ) ቅሬታውን ከታክስ ስሌት ጋር የተገናኘ ከሆነ ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌቱ መሰረት መከፈል ያለበትን እና ተቋውሞ ያላቀረበበትን ታክስ የከፈለ እና ስለመክፈሉም ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ከሆነ፤

(ሐ) በታክስ ውሳኔው ላይ ቅሬታ ቢኖረውም ታክሱን ከፍሎ ቅሬታውን ማቅረብ የመረጠ ከሆነ የተወሰነበትን ታክስ በመክፈል ስለመክፈሉ ማስረጃ ካቀረበ ነው።

6) የሥራ ክፍሉ የቀረበው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ማመልከቻ በአግባቡ አልቀረበም ብሎ ካመነ ቅሬታውን ለመቀበል የሚችል ሲሆን ቅሬታውን ያልተቀበለበትን ምክንያት ለታክስ ከፋዩ ወዲያውኑ በጽሑፍ ምላሽ ይሰጣል፤

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ከፋዩ የቅሬታ ማቅረቢያው ጊዜ ካለፈ ቅሬታውን ማቅረብ ይችል የነበረዉ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያው በደረሰው በ21 (ሃያ አንድ) ቀናት ውስጥ ወይም በታክስ ውሳኔ ላይ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት ጠይቆ የተራዘመለት መሆኑን ተገልጾ የጽሑፍ ማስታወቂያ በደረሰው በ10 (በአስር) ቀናት መሆኑን የሚያሳስብ ምላሽ በጽሑፍ ይሰጣል፤

8) የሥራ በክፍሉ የቅሬታ ማቅረብያ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ በጽሑፍ ከደረሰው ከሚቀጥለው የስራ ቀን ጀምሮ እንዲሁም



Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation

21ኛ ቀን እሁድ ወይም ብሔራዊ በዓል ከሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ጀምሮ ይሆናል፤

9) የሥራ ክፍሉ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችንና ማስረጃዎችን አቅርቦ ያያል ወይም እንዲቀርቡለት ያዛል፣ ቅሬታ አቅራቢው ቀርቦ እንዲያስረዳ ምስክሮችና ባለሙያዎች ጠርቶ ይጠይቃል ወይም ማብራሪያ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፣ ቅሬታው ላይ ውሳኔ የሰጠው የሥራ ኃላፊና ባለሙያ በጽሑፍ ወይም በግንባር ቀርበው መልስ እንዲሰጡ የማድረግ ሥልጣን አለው፤

10) የቀረበው ቅሬታ ሲመረምር በታክስ ስሌት የተመለከተው የታክስ መጠን ሊጨምር ይገባዋል የሚል እምነት የሥራ ክፍሉ ሲኖረው፣ የታክስ ስሌቱ ለሚመለከተው አካል ተመልሶ እንደገና እንዲታይ ለኃላፊው የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

11) የሚቀርቡ የታክስ ውሳኔ ቅሬታዎችን ከመቀበልና አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኝ ከማድረግ በተጨማሪ ቅሬታዎችን ከምንጩ ለማድረቅ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ቅሬታዎች መነሻን መሰረት በማድረግ የትንተና ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ጥናት ያጠናል፣ የህግ እና የአሰራር ማሻሻያ የውሣኔ ሀሳብ ለኃላፊው ያቀርባል፤

12) የሥራ ክፍሉ በቀረበው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ላይ የተወሰነው ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢ በጽሑፍ እንዲደርሰው ያደርጋል፣ በታክስ ስሌት ላይ የቀረበ ቅሬታ ከሆነ ስሌቱን እንዲሻሻል ያደርጋል ይከታተላል፣ እንዲሁም ውሳኔውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ከኃላፊ ጋር በመሆን እንዲወሰድ ያደርጋል።

9. <u>የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ሥልጣን፤</u>

1) ቅሬታ አቅራቢው የፌዴራል ከፍተኛ ግብር ከፋይ ከሆነ የተወሰነበት እና ለቅሬታ ወይም አቤቱታ መነሻ የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድ እና መቀጫን ጨምሮ ከብር 100,000,000 (አንድ መቶ ሚሊየን) በላይ ከሆነ፣

2) ቅሬታ አቅራቢው የፌዴራል መካከለኛ ግብር ከፋይ ከሆነ የተወሰነበት እና ለቅሬታ ወይም አቤቱታ መነሻ የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድ እና መቀጫን ጨምሮ ከብር 50,000,000 (ሃምሳ ሚሊየን) በላይ ከሆነ፤

3) ቅሬታ አቅራቢው የአዲስ አበባ ከፍተኛ ግብር ከፋይ ከሆነ የተወሰነበት እና ለቅሬታ ወይም ለአቤቱታ መነሻ የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድና መቀጫን ጨምሮ ከብር 50,000,000 (ሃምሳ ሚሊየን) በላይ ከሆነ፤

4) ቅሬታ አቅራቢው የአዲስ አበባ መካከለኛ ቁጥር 1 እና 2 ፣ የመርካቶ ቁጥር 1 እና 2 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ግብር ከፋይ ከሆነ የተወሰነበት እና ለቅሬታ ወይም አቤቱታ መነሻ

የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድ እና መቀጫን ጨምሮ ከብር 25,000,000 (ሃያ አምስት ሚሊየን) በላይ ከሆነ፤

5) ቅሬታ አቅራቢው የአዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋይ ከሆነ የተወሰነበት እና ለቅሬታ ወይም አቤቱታ መነሻ የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድን እና መቀጫን ጨምሮ ከብር 5,000,000 (አምስት ሚሊየን) በላይ ከሆኑ የሥራ ክፍሉ ቅሬታዎችን ተቀብሎ በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

10. <u>የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ሥልጣን፤</u>

የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል በዚህ መመሪያ አንቀጽ (9) ለዋናው መሥሪያ ቤት ቅሬታ አጣሪ የስራ ክፍል ከተሰጡት ሥልጣን በታች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

11. <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ሥራ ክፍል ጽ/ቤት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የሥራ ክፍሉ የጽ/ቤት ኃላፊ የሥራ ክፍሉን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ባለሙያዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ጽ/ቤቱ በሰው ኃይል እና በቁሳቁስ እንዲሟላ ያደርጋል፤

2) የሥራ ክፍሉ በሚያደርገው የቅሬታ ማጣራት ሂደት ከቅሬታው ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች ከሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርቡለት ትዕዛዝ ይሰጣል፤ የህግ ወይም የአሠራር ሥርዓት ማብራሪያ የሚያስፈልገው ከሆነ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ያደርጋል፤

3) በማጣራት ሂደት ላይ የሚገኙ ጉዳዮችን በሚመለከት ወይም ከታክስ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውም አካላት መጥራት ሲያስፈልገው በጽሑፍ ወይም በቃል ለመጥራት የሚያስችል ትዕዛዝ ያስተላልፋል፤

4) በሥራ ክፍሉ ተጣርቶ የቀረበ የውሳኔ ሀሳብ በቃለ-ጉባኤ በማስደገፍ ለኃላፊው ያቀርባል፤

5) የሥራ ክፍሉን ባለሙያዎችና ሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ይመዝናል፣ የክፍሉ አፈፃፀም ሪፖርት ለቅርብ የሥራ ኃላፊው እና ሪፖርቱ ሊደርሳቸው የሚገባ ሌሎች አካላት በወቅቱ እንዲላክ ያደርጋል፤

6) ለኃላፊው ቀርቦ የተወሰነ ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢው፣ ቅሬታው ለሚመለከተው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም የሥራ ሂደት እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት በሙሉ በመሸኛ ደብዳቤ የሥራ ክፍሉን የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ጨምሮ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን በመከታተል ውሣኔው ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋል፤

7) የሥራ ክፍሉ ሠራተኞች በማናቸውም ምክንያት ሲጓደሉ አዲስ እንዲመደብ ለሚመለከተው ኃላፊ ያሳውቃል፣

8) ለሥራ ክፍሉ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በማደራጀት ጥናትና ትንተና በማድረግ የችግሩ መነሻና የመፍትሔ ሃሳብ ያካተተ ሪፖርት ለኃላፊ ያቀርባል፣

9) የቅሬታ አቀባበልና አፈታትን ለማፋጠን የሚያስችሉ አሰራሮችን ከሥራ ክፍሉ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ይቀርፃል፣ የሥራ ክፍሉን መልካም ተሞክሮ ቀምሮ ያሰፋል፤

10) ሌሎች ከሥራ ክፍሉ ጋር ተያያዥ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናል፤

## 12. የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍሉ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

1) በግብርና ታክስ ውሳኔ ላይ ለሥራ ክፍሉ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በቅሬታ ማቅረብያ የጊዜ ገደብ መቅረባቸውን በማረጋገጥ ይቀበላል፤

2) ከጽ/ቤቱ ኃላፊ ጋር በመመካከር የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጀል፣ የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤

3) በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት በቀጥታ ይሳተፋል፣ ድምፅ ይሰጣል፤

4) የቀረቡ ቅሬታዎችን በቅሬታ አቅራቢዎቹ ስም በተከፈቱ ማህደሮች መዝግቦ ይይዛል፤

5) የጽ/ቤት ኃላፊው የሰጠውን አመራር በመፈፀምና እና የተዘጋጁ ሪፖርቶች ወጪ በማድረግ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

6) ቅሬታ የቀረበበት ጉዳይ ተጨማሪ ማስረጃ መሰባሰቡን ይከታተላል፣ ደብዳቤዎች በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፣ ቅሬታ አቅራቢዎችና ቅሬታ የቀረበበት አካል በቀረበው ጉዳይ እንዲያስረዳ ቀጠሮ ይሰጣል ይከታተላል፤

7) የውሳኔ ሀሳብ ረቂቅ በማዘጋጀት ተፈርሞ ለኃላፊ በዕለቱ እንዲደርስ ያደርጋል፣ ከኃላፊው ጋር በመመካከር ውሳኔው ለቅሬታ አቅራቢና ቅሬታው ለቀረበበት አካል እንዲደርስ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

8) የኃላፊው ውሳኔ እና የውሳኔው ግልባጭ ለሚመለከታቸው አካላት በአስቸኳይ እንዲደርስ ያደርጋል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

9) የአፈፃፀም ሪፖርት በወቅቱ ተዘጋጅቶ በጽህፈት ቤት ኃላፊው ተፈርሞ ለሚመለከታቸው አካላት በሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ እንዲደርስ ያደርጋል፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 2
Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

10) በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያቀረበው ግለሰብ ወይም ድርጅት ቅሬታው እየታየ መሆኑን በቅሬታ አቅራቢው ሲጠየቅ እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው አካላት በጽሑፍ ይገልፃል፣

11) በክፍሉ ጽ/ቤት ኃላፊ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል፤

## 13. የዋና ዳይሬክተር ወይም በዋና ዳይሬክተር የተወከለው ሰው ኃላፊነት

1) የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ከማለፉ በፊት ታክስ ከፋዩ በታክስ ውሳኔ ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ የማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት ለኃላፊው በጽሑፍ ማመልከቻ ካቀረበ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜውን ለተጨማሪ አስር ቀናት ማራዘም ይችላል፤

2) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ሊራዘም የሚችለው ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታውን በጊዜ ገደቡ ማቅረብ ያልቻለው በራሱ ባልሆነ ወይም/እና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሲሆን ነው፤

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አፈፃፀም በራሱ ያልሆነ ወይም/እና ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው በአገር ውስጥ ወይም የሥራ አድራሻው በሚገኝበት ክልል (ከተማ) አለመኖር እና በአሳማኝ ምክንያት ለመመለስ ያለመቻል፣ በጽኑ ህመም፣ በሕግ ቁጥጥር ስር መዋል፣ በጦርነት፣ በመሬት መንቀጥቀጥ፣ በጎርፍ አደጋ፣ በወረርሽኝ፣ በእሳት ቃጠሎ እና በመሳሰሉ የሰው እና የተፈጥሮ አደጋ እና እራሱ ወይም የቅርብ ቤተሰብ በህይወት መለየት እና የመሳሰሉ ምክንያቶች ናቸው፤

4) ኃላፊው በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ይመረምራል፣ የቀረበውን ቅሬታ በሙሉ ወይም በከፊል በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ ወይም በማሻሻል ውሳኔ ይሰጣል። ውሳኔው በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 53 ንዑስ ቁጥር (4) መሠረት "በቅሬታ ላይ እንደተሰጠ ውሳኔ" ይቆጠራል፤

5) ኃላፊው ታክስ ከፋዩ ቅሬታ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 180 /አንድ መቶ ሰማንያ/ ቀናት ውስጥ አቅራቢው ውሳኔ እንዲያገኝ የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፤

6) የውሳኔ ሀሳቡ የቀረበለት ኃላፊ የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ ሊሽር፣ ሊያፀድቅ፣ ሊያሻሽል ወይም በውሳኔ ሀሳቡ መታየት አለባቸው የሚላቸውን በመግለጽ ተጨማሪ ማጣራት እንዲደረግ ለሥራ ክፍሉ መመለስ ይችላል።

## 14. የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ሥራ ክፍል አጠቃላይ ኃላፊነትና ተጠያቂነት

1) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍሉ የቀረበለትን ቅሬታ በህጉና በማስረጃ ላይ በመመስረት በተፋጠነ መልኩ ግልጽ፣ ፍትሐዊ፣ በህግ የተደገፈ የውሳኔ ሀሳብ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 2
Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፤

2) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የስራ ክፍሉ የሰነዶች ሚስጥራዊነቱ በአግባቡ መጠበቅ፣ አደራጅቶ የመያዝ፣ ሪፖርቶችን ለሚመለከታው አካላት በጊዜ ገደቡ የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

3) የሥራ ክፍሉ ሥራ በማይበዛበት ጊዜ ኃላፊ የሚሰጠውን ተጨማሪ ስራዎች ያከናውናል፣ ለሥራ ክፍሉ ባለሙያዎች በዕቅድ የሚመራ ስራን የማይጎዳ የፈቃድ አሰጣጥ አሰራር ይተገብራል፤

4) ኃላፊው የተሰጠው ውሳኔ ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ያሳውቃል፣የስራ ክፍሉ የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ እንዲደርሰዉ ያደርጋል ፣በታክስ ስሌት ላይ የቀረበ ከሆነ የታክስ ስሌቱን ማሻሻልን ጨምሮ ውሳኔውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ይወስዳል፤

5) ኃላፊው በቅሬታው ላይ የሚሰጠው የውሳኔ ማስታወቂያ የጉዳዩን ዋና ፍሬ ነገሮች፣ ግኝቶች እና ለውሳኔው መሰረት የሆኑትን ምክንያቶቶች እንዲሁም በውሳኔው ካልተስማማ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻል የሚገልጽ መግለጫ ማካተት አለበት፤

6) የሥራ ክፍሉ ሠራተኞች በሥነ-ምግባር እና በሰራተኛ አስተዳዳር ደንብ መሰረት ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን በአግባቡ እየተወጡ እንደሆነ እንዲሁም የሥራ ክፍሉ ሥራ በአግባቡ መከናወኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፤

7) የሥራ ክፍሉ የተጣለበትን ኃላፊነት ባለመወጣት ጥፋት ሰርቶ ቢገኝ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 15. <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ሥራ ክፍል የውሳኔ ሀሳብ አቀራረብ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት፦</u>

1) በእያንዳንዱ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ በሚሰማበት ጊዜ ከክፍሉ አባላት ሁለት ሦስተኛው ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ እንደተሟላ ይቆጠራል፤

2) በተሟላ ምልዓተ-ጉባኤ በአብዛኛው የተደገፈው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ክፍሉ ሃሳብ ሲሆን ድምፁ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ የሥራ ክፍሉ ጽ/ቤት ኃላፊ የተደገፈ ሃሳብ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ክፍሉ የውሳኔ ሀሳብ ይሆናል፤

3) በዋና መሥሪያ ቤት እና በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የሚቋቋመው ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ኃላፊ ቅሬታውን በአግባቡ በማጣራት የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

4) የሥራ ክፍሉ የውሳኔ ሀሳብ የሚባለው በተሟላ ምልዓተ-ጉባኤ በአብዛኛው አባላት የተደገፈው የውሳኔ ሀሳብ የሥራ ክፍሉ የውሳኔ ሀሳብ ሲሆን በውሳኔ አሰጣጥ ድምፁ

እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ በሥራ ክፍሉ ጽ/ቤት ኃላፊ የተደገፈው ሀሳብ የሥራ ክፍሉ የውሳኔ ሀሳብ ይሆናል፤

5) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በውሳኔ አሰጣጡ ከአብዛኛው የተለየ ሀሳብ ያለው አባል የተለየበትን ውሳኔ በቃለ-ጉባኤ እንዲመዘገብለት ይደረጋል። የሥራ ክፍሉ የውሳኔ ሀሳብ ቃለ-ጉባኤ በስብሰባው የተገኙ እና በውሳኔ የተስማሙ አባላት በፊርማ ያረጋግጣሉ፤

6) በሥራ ክፍሉ የሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በኃላፊ ሲጸድቅ የሥራ ክፍሉ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል።

16. <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል የውሳኔ ሀሳብ ይዘት፣</u>

1) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል በታክስ አስተዳዳር አዋጅ አንቀጽ 54 መሰረት የቀረበለትን ቅሬታ በመመርመር የሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ፤

(ሀ) ቅሬታውን በጥልቀት ሲመረምር የለያቸውን ጭብጦችና የደረሰባቸውን ግኝቶች፣ ያሰባሰባቸውን፣ ያገናዘባቸውን ወይም የተመለከታቸውን ዝርዝር ማስረጃዎች (ሰነዶች)፣ አስቀርቦ ያነጋገራቸውንና የጠየቃቸውን ሰዎች አስተያየትና ፍሬ ጉዳዮች፤

(ለ) በቅሬታ አቅራቢ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣ ቅሬታው ድጋፍ ያገኘው በሙሉ ወይም በከፊል ስለመሆኑ፤

(ሐ) በተሰጠው ውሳኔ በሥራ ክፍሉ ሠራተኞች መካከል ልዩነት ካለ ይህንኑ ማካተት ይኖርበታል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቅራቢ ግዴታዎች እና የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት</u>

17. <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ስለማቅረብ</u>

ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 2(34) በፊደል ተራ (ለ)፣(ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ረ)፣ (ሰ) ወይም (ሸ) በተመለከቱ የታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ (18) የተመለከቱትን ግዴታዎች ካሟላ በታክስ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ማስታወቂያ ማቅረብ ይችላል፤

18. <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቅራቢ ግዴታዎች</u>

1) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቅራቢው በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 2(34) በፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ረ)፣ (ሰ) ወይም (ሸ) በተደነገጉት መሰረት በታክስ ውሳኔ ላይ

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

ቅሬታ ካለው የታክስ ውሳኔ በጽሑፍ በተሰጠው በ21 (ሃያ አንድ) የሥራ ቀናት ውስጥ የቅሬታ ማስታወቂያውን ለክፍሉ ማቅረብ አለበት፤

2) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቅራቢው የሚቀርበው ቅሬታ በታክስ ስሌት ማሻሻያ ላይ ከሆነ በመጀመሪያው የታክስ ስሌት በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በዚህ ላይ በተደረገ ማሻሻያ ላይ ከሆነ በመጀመሪያው የቅሬታ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፤

3) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቅራቢው የሚቀርበው ቅሬታ ባልተስማማበት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ላይ እንጂ በተስማማበት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንደማይችል የመገንዘብ፤

4) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቅራቢው በታክስ ከፋዩ የሚቀርበው ቅሬታ በዚሁ መመሪያ የተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ የመቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## 19. የታክስ ውሳኔ የቅሬታ ማስታወቂያው ይዘት

1) የቅሬታው ማስታወቂያ የቅሬታውን ፍሬ ነገር እና ምክንያቶች መያዝ አለበት፤

2) የቅሬታ አቅራቢው ስምና አድራሻ፣ ቀን፣ ቅሬታ የቀረበበት ጉዳይ፣ ውሳኔው የተሰጠበትን ቀን፣ ውሳኔ ሰጪው ቅርንጫፍ ጽ/ቤትና የስራ ሂደት ስም ማካተት አለበት፤

3) ቅሬታ አቅራቢው የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የምስክር ወረቀት፣ እንዲሁም ጉዳዩ በታክስ ወኪሉ የሚቀርብ ከሆነ የወኪሉ ፈቃድ፣ ቅሬታ አቅራቢ ውክልና የሰጠበት ማስረጃ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት፤

4) የቀረበውን ቅሬታ የሚያስረዱ አግባብ ያላቸው ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች ከቅሬታ ማስታወቂያው ጋር በአባሪነት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 20. የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ማስታወቂያ የሚቀርብበት ቀንና አቀራረብ

1) የቅሬታ ማስታወቂያ የቀረበበት ቀን የሚባለው ለዋና መ/ቤት ወይም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሪከርድ ሥራ አመራር የሥራ ክፍል በኩል ገቢ ተደርጎ የሚቀርብ ሲሆን ቅሬታው ተቀባይነት አገኘ የሚባለው የክፍሉ ባለሙያ ፀሐፊ ፈርሞ የተቀበለበት ቀን ነው፡፡

2) የቅሬታ ማስታወቂያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ (18) መሰረት ቅሬታውን ቅሬታ አቅራቢው ድርጅት፣ ግለሰብ ወይም በሚወክለው የታክስ ወኪል ተፈርሞ መቅረብ አለበት

21. **የጊዜ ገደብ**

1) በታክስ ውሳኔ ላይ ታክስ ከፋዩ ላቀረበው ቅሬታ ባለሥልጣኑ ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 180 (አንድ መቶ ሰማንያ) ቀናት ዉስጥ ለቅሬታው ውሳኔ መስጠት አለበት፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ባለሥልጣኑ ውሳኔ ካልሰጠ ቅሬታ አቅራቢው የጊዜ ገደቡ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቅረብ ይችላል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

22. **የማስረዳት ኃላፊነት**

ከታክስ ውሳኔ ጋር በተያያዘ በሚቀርብ ማንኛውም ቅሬታ በሚደረግ የክርክር ሂደት ትክክል አለመሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት የቅሬታ አቅራቢው ነው።

23. **የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች**

1) የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያና የአሰራር መመሪያ ቁጥር 91/2006 እና

2) የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያና የአሰራር መመሪያ ቁጥር 91/2006ን ለማሻሻል የወጣው መመሪያ ቁጥር 113/2008 ተሽሯል።

3) ቀደም ሲል የነበሩ አሰራሮችና ልምዶች ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ከሆኑ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

24. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የቀረቡ እና ውሳኔ ያላገኙ ቅሬታዎች በዚህ መመሪያ መሰረት ውሳኔ እንዲያገኙ ይደረጋል።

25. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 01 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል።

አዲስ አበባ ነሀሴ 2009 ዓ.ም

ሞገስ ባልቻ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር

4/12/09
የሕግ ረቂቅና ስልጠና ቡድን አስተባባሪ